የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፯ ቀን ፪ሺ፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 2
ADDIS ABABA 16th December, 2009

ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፰/፪ሺ፪ ዓ.ም**

ለአዲስ አበባ-አዳማ የፍጥነት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………ገጽ ፭ሺ፩፻፭

**CONTENTS**

**Proclamation No. 658/2009**

Export-Import Bank of China Loan Agreement for Addis Ababa Adama Toll Motorway Design Project Ratification Proclamation Page 5105

**አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፰/፪ሺ፪**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቻይና ኤክስፖርት ኤምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለአዲስ አበባ-አዳማ የፍጥነት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፫፻፵፱ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /ሦስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፰ ቀን ፪ሺ፱ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፲፯ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም ባካሔደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**PROCLAMATION NO. 658/2009.**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF CHINA**

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China stipulating that the Export-Import Bank of China provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding USD 349,000,000 (three hundred forty nine million United States Dollars) for financing the Addis Ababa Adama Toll Motorway Design and Build Road Project, was signed in Addis Ababa on the 8th day of November 2009;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financial Agreement at its session held on the 26th day of November, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ-አዳማ የፍጥነት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፰/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፰ ቀን ፪ሺ፱ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር PBC No. 2009 (37) Total No. (99) የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፫፻፵፱ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /ሦስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጀ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፯ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Export-Import Bank of China Loan Agreement for Addis Ababa Adama Toll Motorway Design Project Ratification Proclamation No. 658/2009."

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement PBC Number 2009(37) Total No. (99) signed in Addis Ababa on the 8th day of November 2009 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of USD 349,000,000 (three hundred forty nine million United States Dollar) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of December, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**